# ሰላም ለፍልሰተ ሥጋኪ (ዘአኀተሞ ገብረ ሥላሴ)

| ሰላም ለፍልሰተ ሥጋኪ-ግዕዝ | ሰላም ለፍልሰተ ሥጋኪ በአማርኛ |
| --- | --- |
| ፩. ሰላም ለፍልሰተ ሥጋኪ ምስለ ነፍስኪ ኢመዋቲ፣ በተሰናዕዎ አሐቲ፣ ድንግል በክልኤ ማርያም ወለተ ማቲ፣ ሐመረ ተርሴስ ዘሰሎሞን አንቲ፣ እንተ አእተዉ ጠቢባን ወርቀ አፌዝ ባቲ፡፡ | 1. ለፍልሰተ ሥጋኪ፡- ጠቢባን የአፌዝን ወርቅ የሚያመላልሱባት በንጉሥ ሰሎሞን ወደብ የምትገኝ በኹለት ወገን ድንግል የኾንሽ የከበረ ማቲ ልጅ እመቤቴ ድንግል ማርያም ሆይ! በሞት ተይዞ ካልቀረ ሰውነትሽ ጋራ በአንዲት ስምምነት ለሚኖር ቅዱስ ፍልሰተ ሥጋሽ ሰላምታ ይገባሻል፡፡ |
| ፪. ሰላም ለፍልሰተ ሥጋኪ መካነ ፍሥሓ ወኑዛዜ፣ ኀበ ይረስእዎ ለላሕ ወኢይሔልይዎ ለትካዜ፣ ማርያም ህለት ውስተ ልበ አምላክ እምቅድመ ጊዜ፣ ትፍሥሕትሰ ተፈሣሕኩ በፍልሰትኪ ይእዜ፣ ገጸ ዚአኪ እሬኢ ማእዜ፡፡ | 2. ለፍልሰተ ሥጋኪ፡- ከዘመን አስቀድሞ በአምላክ ልቡና የነበርሽ ለቅሶን የሚረሱበት ትካዜንም የማያስቡበት የመጽናናትና የደስታ መገኛ ለኾነ ፍልሰተ ሥጋሽ ሰላምታ ይገባል፣ እመቤቴ ድንግል ማርያም ሆይ! በፍልሰተ ሥጋሽ ዛሬ እጅግ ተደሰትሁ፣ ገጸ ምሕረትሽንስ የማየው መቼ ይኾን! |
| ፫. ሰላም ለፍልሰተ ሥጋኪ ውስተ ልበ ሰብእ ዘኢተኀለየ፣ እንዘ ትትአጸፊ ወትለብሲ ዕበየ፣ ማርያም ሥጋኪ ዘተመሰለ ባሕርየ፣ ተኀፍረ ሞት አኮኑ ሶበ ነጸረ ወርእየ፣ አመ በደመና ብሩህ ተዐርግ ሰማየ፡፡ | 3. ለፍልሰተ ሥጋኪ፡- በሰው ልቡና ያልታሰበ ዕበየ ቅድስናን ተጐናጽፈሽ ለተፈጸመ ፍልሰተ ሥጋሽ ሰላምታ ይገባል፣ እመቤቴ ቅድስት ድንግል ማርያም ሆይ! እንደ ዕንቍ የሚያበራ ቅዱስ ሥጋሽ በብሩህ ደመና ተከብቦ ወደ ሰማይ ሲያርግ አይቶ መልአከ ሞት እጅግ አፈረ፡፡ |
| ፬. ሰላም ለፍልሰተ ሥጋኪ እግዚአብሔር ዘባረካ፣ ወአልዐለ ክብራ እምፍልሰተ ሄኖክ ወልደ ባረካ፣ ማርያም ፍሥሕት ወብርህት እምነ ዋካ፣ በእንቲኣኪ ይገብሩ ውስተ ሰማያዊት ታዕካ፣ ነገደ መላእክት አእላፍ ሱባዔ ፋሲካ፡፡ | 4. ለፍልሰተ ሥጋኪ፡- አእላፍ ነገደ መላእክት በሰማያዊት ኢየሩሳሌም ውስጥ እጅግ የበዛ ምስጋናን የሚያመሰግኑሽ ደስታን የተመላሽ ከብርሃን ይልቅ እጅግ የምታበሪ እመቤቴ ቅድስት ድንግል ማርያም ሆይ! እግዚአብሔር ስለባረካት ከባረካ ልጅ ነቢይ ሄኖክ ዕርገተ ሥጋ ይልቅ ክብሯ ከፍ ከፍ ለአለ ፍልሰተ ሥጋሽ ሰላምታ ይገባል፡፡ |
| ፭. ሰላም ለፍልሰተ ሥጋኪ ዘኢይቀብል ሞገሱ፣ ወኢይነጽፍ ባሕረ ተውዳሱ፣ ማርያም ታዕካ ለእግዚአብሔር ጽርሐ መቅደሱ፣ ተባህሉ በሰማያት እለ ኪያኪ አፍለሱ፣ ማርያምሰ እንተ በምድር ታንሶሱ፡፡ | 5. ለፍልሰተ ሥጋኪ፡- ሞገሰ ቅድስናው ለማይጐድል ባሕረ ምስጋናውም ለማይነጥፍ ፍልሰተ ሥጋሽ ሰላምታ ይገባል፣ የእግዚአብሔር የቅድስና አዳራሹ እመቤቴ ቅድስት ድንግል ማርያም ሆይ! ፍልሰተ ሥጋሽን የአጀቡ ነገደ መላእክት ‹ድንግል ማርያም በምድር ኹሉ የከበረች› ናት እያሉ በሰማያት አመሰገኑ፡፡ |

፮. ሰላም ለፍልሰተ ሥጋኪ ዘአፈድፈደ ስባሔ፤ እምፍልሰተ ያዕቆብ ዐርከ ኤሎሂ፤ ማርያም ቀንሞስ ማርያም አፈወ ርኄ፤ እንዘ ብርሃነ ይለብሱ ወይትዐጸፉ ሱራሔ፤ በዓለ ፍልሰትኪ መላእክት ሰበኩ ኵለሄ፡፡

፯. ሰላም ለፍልሰተ ሥጋኪ ስቡሐ ዘተሰብሐ፤ እምሥነ ፀሐይ ወወርኅ ሥነ ስብሐቲሁ አብርሃ፤ እንበሌኪ ድንግል ወእንበለ ወልድኪ በኵረ ፍሥሓ፤ አልቦ ለሞት ማእሰሪሁ ዘፈትሐ፤ ወሙታነ እምሲኦል አንቅሐ፡፡

፰. ሰላም ለፍልሰተ ሥጋኪ እምዓለመ መትሕት ኀላፊ፤ ውስተ ኪሩብ ተሃሉ እንዘ የዐቅባ ሱራፊ፤ ማርያም ምዕዝት እምሥነ ጽጌያት ዘወርኀ ታውፊ፤ ናሁ ተሰጠምኩ ውስተ ባሕረ መንሱት ጸናፊ፤ በሐመረ ንጽሕኪ ወትረ ኪያየ ሐድፊ፡፡

፱. ሰላም ለፍልሰተ ሥጋኪ ለሊቀ ካህናት ዘአደሞ፤ መሥዋዕተ መድኀኒት ያዕርግ ቅድስተ ቅዱሳን ቀዊሞ፤ ለመልአከ ሞት ፀዋግ መልአከ በቀል ወተቀይሞ፤ ሚ መጠነ አድወየ ወሚ መጠነ አሕመሞ፤ ሞገሰ ፍልሰትኪ ማርያም ዘአምላክ ኀተሞ፡፡

፲. ሰላም ለፍልሰተ ሥጋኪ ዘአጥናን ኀይሉ፤ ወአኢናዎን መዝራዕተ ሣህሉ፤ ማርያም ዝክርኪ ለትውልደ ትውልድ ዘይሄሉ፤ አምጻኢተ ምሕረት አንቲ ለኃጥአነ ምድር ኵሉ፤ ቡርክት ማርያም ለክርስቶስ አባሉ፡፡

፲፩. ሰላም ለፍልሰተ ሥጋኪ በሰዋስወ ብርሃን ምጡቅ፤ ከመ ትኩኒዮሙ እመ ለኅሩያን ደቂቅ፤ ተሣይጥኒ ማርያም በንዋየ ሣህልኪ ወርቅ፤ ከመ ይሣየጡ አመ ዕለተ

6. ለፍልሰተ ሥጋኪ፡- ከእግዚአብሔር ወዳጅ ከያዕቆብ ፍልሰት ይልቅ ምስጋናን ለተመላ ፍልሰተ ሥጋሽ ሰላምታ ይገባል፤ ቀንሞስ ርኄ እንደተሰኙ ሽቱዎች ደስ የምታሰኚ እመቤቴ ቅድስት ድንግል ማርያም ሆይ! ነገደ መላእክት ብርሃን ለብሰው ብርሃን ተጐናጽፈው በዓለ ፍልሰትሽን ዘወትር ያከብራሉ፡፡

7. ለፍልሰተ ሥጋኪ፡- እመቤቴ ድንግል ማርያም ሆይ! የደስታ መገኛ ከኾነ ልጅሽ በቀር የሞት ማሰሪያን የፈታ፤ ሙታንንም ከሲኦል ያወጣ የለምና ሰማያዊ ክብሩ ከፀሐይና ከጨረቃ ይልቅ እጅግ ለሚያበራና ፈጽሞ ለተመሰገነ ፍልሰተ ሥጋሽ ሰላምታ ይገባሻል፡፡

8. ለፍልሰተ ሥጋኪ፡- ከታችኛው ኀላፊ ዓለም ይልቅ በሰማያዊ ዙፋን ቅዱስ ሱራፌ እየጠበቃት ለምትኖር ፍልሰተ ሥጋሽ ሰላምታ ይገባል፤ ከወርኀ ታኅሣሥ የአበባ ፍካት ይልቅ ደስ የምታሰኚ እመቤቴ ድንግል ማርያም ሆይ! ከጥፋት ባሕር ዳርቻ እነሆ ሠጥሜያለሁና በንጽሕናሽ መርከብ ዘወትር እኔን አድኚኝ፡፡

9. ለፍልሰተ ሥጋኪ፡- በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ ቆሞ የድኅነት መሥዋዕትን ያሳርግ ዘንድ ሊቀ ካህናት ክርስቶስን ደስ ለአሰኘ የሥጋሽ ፍልሰት ሰላምታ ይገባል፤ እመቤቴ ድንግል ማርያም ሆይ! አምላክ የአከበረው ሞገሰ ፍልሰትሽ በቀልና ቂምን የተመላ ክፉ መልአከ ሞትን እጅግ አሠቃይቶ አጠፋው፡፡

10. ለፍልሰተ ሥጋኪ፡- ምስጋና ኀይሉ ቅድስናም የይቅርታ ክንዱ ለኾነ ፍልሰተ ሥጋሽ ሰላምታ ይገባል፤ የክርስቶስ እናቱ የተባረክሽ እመቤቴ ድንግል ማርያም ሆይ! ለምድር ኃጥአን ኹሉ ምሕረትን የምታሰጭ ነሽና መታሰቢያሽ ለዘለዓለም ይኖራል፡፡

11. ለፍልሰተ ሥጋኪ፡- ለተመረጡ ቅዱሳን ረዳት እናታቸው ትሆኚ ዘንድ በረኸም የብርሃን መሰላል ለተከወነ ፍልሰተ ሥጋሽ ሰላምታ ይገባል፤ እመቤቴ ድንግል ማርያም ሆይ! አምስቱ የአዕዋፍ ወገኖች በኹለት ዲናር ይዋጁ እንደነበር አንቺም እኔን ልጅሽን በተወደደ

| | |
|---|---|
| ፍትወት ወጻሕቅ፤ ዘመደ አዕዋፍ ኀምስ በክልኤ ጸሪቅ፡፡ | የአማላጅነትሽ ገንዘብ ዋጅተሽ ታድኝኝ ዘንድ እማፀናለሁ፡፡ |
| ፲፪. ሰላም ለፍልሰተ ሥጋኪ እግዚአብሔር ዘተወሐዳ፤ ወተካፈለ ክበዳ፤ በፍልሰትኪ ማርያም ለኢየሩሳሌም ምድረ ይሁዳ፤ ስኂነ ተዝካር ወአፈወ ዕጣን ጸዐዳ፤ ነገሥተ ተርሴስ ወደስያት ያበውኡ ጋዳ፡፡ | 12. ለፍልሰተ ሥጋኪ፡- እግዚአብሔር ወልድ ቀድሶና አክብሮ ለተዋሐዳት የሥጋሽ ፍልሰት ሰላምታ ይገባል፤ እመቤቴ ድንግል ማርያም ሆይ! በይሁዳ አውራጃ ኢየሩሳሌም ለተከወነ ቅዱስ ፍልሰትሽ የተርሴስና የደስያት ነገሥታት የመታሰቢያ ሽቱንና ነጭ ዕጣንን እጅ መንሻ አድርገው ያቀርባሉ፡፡ |
| ፲፫. ሰላም ለፍልሰተ ሥጋኪ እግዚአብሔር ዘአልዐሎ፤ እምፍልሰተ ኤልያስ ነቢየ ሴሎ፤ ውስተ ብሔረ ጽድቅ ሰድኒ ማርያም በክነፈ ዓውሎ፤ ለምንት ሊተ በፍግዓ ወበጥዒና እዴሎ እንዘ ይዴግነኒ ሞት ዘይኄንን ኵሎ፡፡ | 13. ለፍልሰተ ሥጋኪ፡- ልዑል እግዚአብሔር ከነቢየ ሴሎ ከቅዱስ ኤልያስ ፍልሰት ይልቅ ከፍ ከፍ ለአደረገው ቅዱስ ፍልሰተ ሥጋሽ ምስጋና ይገባል፤ እመቤቴ ቅድስት ድንግል ማርያም ሆይ! በክንፈ ረድኤትሽ ወደ ጽድቅ ሥፍራ ውሰጂኝ እንጂ ኹሉን የሚረታ ሞት በኋላየ እየተከተለኝ በዚኽ ዓለም እንደምን በደስታና በጤና እኖራለሁ! |
| ፲፬. ሰላም ለፍልሰተ ሥጋኪ ውስተ ብሔር ሣዑር፤ እንተ ኬንያሃ ወገባሪሃ እግዚአብሔር፤ ማርያም ፍትሕኒ እምግብርናተ ሞት መሪር፤ ሶበሰ ትፈቅዲ ንግሥተ ሰማያት ወምድር፤ ኢይሰዐነኪ አግእዞቱ ለኃጥእ ገብር፡፡ | 14. ፈጣሪዋ እግዚአብሔር ወደአዘጋጀላት ምድረ ገነት ለዐረገች ፍልሰተ ሥጋሽ ሰላምታ ይገባል፤ ንግሥተ ሰማያት ወምድር እመቤቴ ድንግል ማርያም ሆይ! ብትወጂስ ኀጢአተኛን ከኀጢአቱ መጠበቅ ይቻልሻልና ከሚያስጨንቅ የሞት ቁራኝነት ታድኚኝ ዘንድ እለምንሻለሁ፡፡ |
| ፲፭. ሰላም ለትንሣኤ ሥጋኪ እምትንሣኤ ክርስቶስ መንታ፤ ርእሶ ሕያወ እንተ ኀብአ ውስቴታ በጽላሎትኪ ክድንኒ ማርያም ርግብ ኤፍራታ፤ ወሠውርኒ በአክናፍኪ አመ ይከውን ሐተታ፤ ወአመ ታገብእ ምድር ዘነሥአት ማሕፀንታ፡፡ | 15. ለትንሣኤ ሥጋኪ፡- በከበረች የክርስቶስ ትንሣኤ ጥላ ውስጥ ሕያው ራሱን ለአስጠጋ ፍልሰተ ሥጋሽ ሰላምታ ይገባል፤ የኤፍራታ ርግብ እመቤቴ ድንግል ማርያም ሆይ! በመጨረሻው ዘመን ስጠየቅ ምድርም የተሰጣትን አደራዋን በመለሰች ጊዜ በአማላጅነትሽ ጥላ ሸፍነሽ በአክናፈ ምሕረት ሠውሪኝ፡፡ |
| ፲፮. ሰላም ለዕርገተ ሥጋኪ ዘተወጥነ ቦቱ፤ ዕርገተ ቅዱሳን ሕዝብ እለ ኪያኪ አእኰቱ፤ ለሊቀ ካህናት አሮን ማርያም ሠርጐ ትርሲቱ፤ ሥዑለ ይኩን በልብስኪ እንተ በላዕሉ ወታሕቱ፤ ፍሬ ከናፍር ወአፍ ውዳሴኪ ዝንቱ፡፡ | 16. ለዕርገተ ሥጋኪ፡- የሊቀ ካህናት አሮን የክብሩ ሽልማት እመቤቴ ድንግል ማርያም ሆይ! ይኽ የከንፈሬና የአፌ ፍሬ ምስጋናሽ በላይም በታችም በተገናጸፍሽው ልብሰ ርኅራኄሽ የተሣለ ይሆን ዘንድ አንቺን ለአመሰገኑ ቅዱሳን ጻድቃን ዕርገት ኹሉ ምክንያት ለኾነ ዕርገተ ሥጋሽ ሰላምታ ይገባል፡፡ |

<table>
<tr>
<td>ኦ እግዝእትየ ማርያም ዕቀብኒ ወአድኅንኒ እመከራ ሥጋ ወነፍስ ሊተ ለገብርኪ..... ወትረ በኵሉ ጊዜ ወበኵሉ ሰዓት ለዓለመ ዓለም አሜን፡፡<br><br>አቡነ ዘበሰማያት...<br><br>✞ ✞ ✞</td>
<td>እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ሆይ! ኃጥእ ልጅሽን..... ከመከራ ሥጋ ከመከራ ነፍስ ዘወትር በየጊዜውና በየሰዓቱ አድኚኝ፤ ጠብቂኝም፤ ለዘለዓለሙ አሜን፡፡<br><br>አባታችን ሆይ...<br><br>✞ ✞ ✞</td>
</tr>
</table>

<table>
<tr>
<th colspan="2">መልክዐ ፍልሰታ</th>
</tr>
<tr>
<td><u>መልክዐ ፍልሰታ-ግእዝ</u><br><br>፩. ሰላም ለኪ ማርያም እምነ፤ መግመሪተ ነድ ርስነ፤ ዓምደ ባሕርይ ዘኢ.ተአምሪ ጸኒነ፤ ድንግልናተ ፪ተ ምልዐ ሥጋኪ ተከድነ፤ አፍለሰኪ ወልድ ሉዓሌ መካነ፡፡<br><br>፪. ምንተ አዐሥዮ ለእግዚአብሔር አሐተ፤ በእንተ ኵሉ ዘገብረ ሊተ፤ ረስዩኒ እሙ አሥምሮ ግብተ፤ ማርያም እግዝእትየ ዘሜጥሮ እሳተ፤ ድኅረ በጽሐ ልሳኑ ዘለኪ ቤተ፡፡<br><br>፫. አፉየ አስተንፈሰ፤ ወልሳንየ አልኖሰሰ፤ ለክብረ ፍልሰትኪ ድንግል ሶበ አቁርብ ተውዳሰ፤ ማርያም ዘኮንኪ ቅድስተ ቅዱሳን መቅደሰ፤ በቅድሜኪ እግዝእትየ እመ ረከብኩ ሞገሰ፤ በየማንኪ ባርክኒ ሥልሰ፡፡<br><br>፬. ሰላም ለፍልሰተ ሥጋኪ ምስለ ነፍስኪ ኢ.መዋቲ፤ በተሰናዕዎ አሐቲ፤ ድንግል በይኤ ማርያም ወለተ ማቲ፤ ሐመረ ተርሴስ</td>
<td><u>መልክዐ ፍልሰታ በአማርኛ</u><br><br>1. ሰላም ለኪ፡- እናታችን ማርያም ሆይ! ሰላም ለአንቺ ይሁን፤ መለኮትን የተሸከምሽ መጉደልን የማታውቂ በሁለቱ ድንግልናዎችሽ መላ አካልሽ ተሸፈነ፡፡<br><br>2. ምንተ አዐሥዮ፡- ይህን ሁሉ ለአደረገልኝ ለእግዚአብሔር ምን እከፍለዋለሁ! ነበልባሉ ወደ ቤትሽ ከደረሰ በኋላ እሳትን የመለስሽ የጌታ እናቱ እመቤቴ ማርያም ሆይ! ልጅሽን አገለግለው ዘንድ የበቃሁ አድርጊኝ፡፡<br><br>3. ለክብረ ፍልሰትኪ፡- አንደበቴ ተናገረ፤ አፌም ዘመረ፤ ለዕርገትሽ ክብር ዝማሬን በአቀረብሁ ጊዜ ቅድስተ ቅዱሳን መቅደስ የሆንሽ እመቤቴ ማርያም ሆይ! በፊትሽስ ባለሟልነትን ባገኝ በቀኝ እጅሽ ሦስት ጊዜ ባርኪኝ፡፡<br><br>4. ለፍልሰተ ሥጋኪ፡- ከማትሞት ነፍስሽ ጋር በአንድነት በመስማማት ለሥጋሽ ማረግ ሰላምታ ይገባል፤ የማቲ ልጅ ማርያም በሁለት ወገን ድንግል ነሽ፡፡ ጠቢባን በውስጧ የያፌዝን (የአፌርን) ወርቅ</td>
</tr>
</table>

| | |
|---|---|
| ዘሰሎሞን አንቲ፤ እንተ አእተው (አእተውዋ) ጠቢባን ወርቀ ያፌዝ (ኦፌር) ባቲ፡፡ | ያስቀመጡባት አንዷት የሆነች የሰሎሞን የተርሴስ መርከብ አንቺ ነሽ፡፡ |
| ፭. ሰላም ለፍልሰተ ሥጋኪ መካነ ፍሥሓ ወኑዛዜ፤ ኀበ ኢይሬእይዎ ለላህ ወኢይሔልይዎ ለትካዜ፤ ማርያም ህሉት ውስተ ልበ አምላክ እም ቅድመ ጊዜ፤ ትፍሥሕተስ ተፈሣሕኩ በፍልስትኪ ይእዜ፤ ገጸ ዚአኪ እሬኢ ማእዜ፡፡ | 5. ለፍልሰተ ሥጋኪ፡- ልቅሶን ወደማያዩበት ኀዘንን ወደማያስቡበት ወደ መጽናናትና ወደ ደስታ ቦታ ለሥጋሽ ማረግ ሰላምታ ይገባል፤ እመቤታችን ከጊዜና ከዘመን አስቀድማ በእምላክ ልቡና ታስባ ትኖር ነበረች፡፡ ደስታንስ ዛሬ በማረግሽ ተደሰትሁ፤ እመቤቴ ማርያም ሆይ! ፊትሽን ግን የማየው መቼ ነው? |
| ፮. ሰላም ለፍልሰተ ሥጋኪ እግዚአብሔር ዘባረካ፤ ወአልዓለ ክብራ እም ፍልሰተ ሄኖክ ወልደ ባረካ፤ ማርያም ስብሕት ወብርህት (ፍሥሕት) ዕለተ ዋካ፤ ይገብሩ በእንቲአኪ ውስተ ሰማያዊት ታዕካ፤ ነገደ መላእክት አእላፍ ሱባዔ ፋሲካ፡፡ | 6. ለፍልሰተ ሥጋኪ፡- ከባረካ ልጅ ከሄኖክ ዕርገት ይልቅ እግዚአብሔር አብዝቶ ክብሯን ከፍ ለአደረገውና ለባረካት ለሥጋሽ ዕርገት ሰላምታ ይገባል፤ የከበርሽና የምታበሪ የብርሃን ቀን እመቤታችን ሆይ! የብዙ ብዙ የሆኑ የመላእክት ወገኖች ስለ አንቺ በሰማያዊት አዳራሽ እጽፍ ድርብ ተድላ ደስታን ያደርጋሉ፡፡ |
| ፯. ሰላም ለፍልሰተ ሥጋኪ ዘኢይቀብል ሞገሱ፤ ወዘኢይነጽፍ ባሕረ ተውዳሱ፤ ማርያም ታዕካ ለእግዚአብሔር ጽርሐ መቅደሱ፤ ተባሂሉ በሰማያት እለ ኪያኪ አፍለሱ፤ ማርያምሰ እንተ በምድር ታንሶሱ፡፡ | 7. ለፍልሰተ ሥጋኪ፡- የምስጋናው ባሕር ለማይነጥፍ ሞገሱም ለማይጎድል ለአካልሽ ዕርገት ሰላምታ ይገባል፤ የእግዚአብሔር መቅደስ ማርያም ሆይ! አንቺን ወደ ሰማያት ያሳረጉሽ መላእክት ማርያም ግን በምድር ትመላለስ ነበረች አሉ፡፡ |
| ፰. ሰላም ለፍልሰተ ሥጋኪ ዘአፍድፈደ ስባሔ፤ እም ፍልሰተ ኤልያስ ዓርከ ኤሎሄ፤ ማርያም ቀንሞስ ማርያም አፈወ ርኄ፤ እንዘ ብርሃነ ይለብሱ ወይትዓጸፉ ሡራሔ፤ በዓለ (ሞገሠ) ፍልሰትኪ መላእክት ሰበኩ ዙለሄ፡፡ | 8. ለፍልሰተ ሥጋኪ፡- ከእግዚአብሔር ወዳጅ ከኤልያስ ዕርገት ይልቅ ምስጋናን ለአበዛው ለአካልሽ ዕርገት ሰላምታ ይገባል፡፡ ርኄና ቀንሞስ የተባሉ ሽቶዎች ምሳሌዎችሽ የሆኑ እመቤታችን ሆይ! መላእክት ፍጹም ብርሃንን ለብሰው የዕርገትሽን በዓል ሁልጊዜ ሰበኩ፡፡ |
| ፱. ሰላም ለፍልሰተ ሥጋኪ ውስተ ልበ ሰብእ ዘኢተሐለየ፤ እንዘ ትትዓጸፊ ጸጋ ወትለብሲ ዕበየ፤ ማርያም ሥጋኪ ዘተመሰለ ባሕርየ፤ ተኃፍረ (ተሐውከ) ሞት አኮኑ ሶበ ነጸረ ወርእየ፤ እንዘ በደመና ብሩህ የዓርግ ሰማየ፡፡ | 9. ለፍልሰተ ሥጋኪ፡- ገናናነትን ስትጎናጸፊ እና ጸጋን ስትለብሺ በሰው ልብ ላልታሰበ ለአካልሽ ዕርገት ሰላምታ ይገባል፤ ሥጋሽ በዕንቍ የተመሰለልሽ እመቤታችን ሆይ! ሥጋሽ በብሩህ ደመና ላይ ተቀምጦ ወደ ሰማያት ሲያርግ አይቶ ዲያብሎስ አፈረ፤ ኀሰቀለ (ታወከ)፡፡ |
| ፲. ሰላም ለፍልሰተ ሥጋኪ ስቡሐ ዘተሰብሐ፤ እምነ ፀሐይ ወወርኀ ሥነ ስብሐቲሁ አብርሀ፤ እንበሌኪ ድንግል ወእንበለ ወልድኪ በኵረ | 10. ለፍልሰተ ሥጋኪ፡- የክብሩ ፀዳል ከፀሐይና ከጨረቃ ይልቅ ላበራውና ምስጋናን ለተመሰገነው ለአካልሽ ዕርገት ሰላምታ ይገባል፤ ድንግል ሆይ! ያለ አንቺና ያለ ደስታሽ በኵር ልጅሽ ያለ ክርስቶስ የሞትን ማሠሪያ የፈታ ሙታንንም ከመቃብር ያስነሣ የለም፡፡ |

ፍሥሓ፤ አልቦ ለሞት ማእሠሪሁ ዘፈትሐ፤ ወሙታነ በሲኦል አንቅሐ፡፡

፲፩. ሰላም ለፍልሰተ ሥጋኪ ለሊቀ ካህናት ዘአደሞ፤ መሥዋዕተ መድኃኒት ያዕርግ ቅድስተ ቅዱሳን ቀዊሞ፤ ለመልአከ ሞት ጸዋግ መልአከ በቀል ወተቀይሞ፤ ሚ መጠነ አድወዮ ወሚ መጠነ አሕመሞ፤ በዓለ (ሞገስ) ፍልሰትኪ ማርያም ዘአምላክ ኀተሞ፡፡

፲፪. እም ዓለመ መትሕት ኃላፊ፤ ውስተ ዓውደ ኪሩብ ተሃሉ እንዘ የዓቅባ ሱራፊ፤ ማርያም ስብሕት (ምዕዝት) እምነ ጽጌያት ዘወርኀ ታውፊ፤ ናሁ ተሰጠምኩ ውስተ ባሕረ ጽልመት ጸናፊ፤ በሐመረ ንግሥኪ (ንጽሕኪ) ወትረ ኪያየ ሐድፊ፡፡

፲፫. ዘአጥናን ኃይሉ ወአኤናዎን መዝራዕተ ሣህሉ፤ ዝክርኪ (ሣህልኪ) ለትውልደ ትውልድ ዘይሄሉ፤ አምጻኢተ ምሕረት ለኃጥአነ ምድር ኵሉ፤ ወብፅዕት ማርያም ለክርስቶስ አባሉ፡፡

፲፬. ሰላም ለፍልሰተ ሥጋኪ እግዚአብሔር ዘተወሐዳ፤ ወተካፈለ ክበዳ፤ ለፍልሰትኪ ድንግል ለኢየሩሳሌም በዓውዳ፤ ስኂነ ተዝካር ወአፈወ እፍረት ፀዐዳ፤ ነገሥተ ተርሴስ ወደስያት ያበውኡ ጋዳ፡፡

፲፭. ሰላም ለፍልሰተ ሥጋኪ እግዚአብሔር ዘአልዓሎ፤ እም ፍልሰተ ኤልያስ ነቢየ ሴሎ፤ ውስተ ብሔረ ጽድቅ ሰድኒ ማርያም በክነፊ አውሎ፤ ለምንት አነ በፍግዓ ወበጥዒና እዴሎ፤ እንዘ ይዴግነኒ ሞት ዘይኄንን ኵሎ፡፡

፲፮. ሰላም ለፍልሰተ ሥጋኪ በሰዋስወ ብርሃን ምጡቅ፤ ከመ ትኩኒዮሙ እሙ ለኅሩያን ደቂቅ፤ ተሣየጥኒ ማርያም በንዋየ ሣህልኪ ጽድቅ፤ ከመ ይሣየጡ አመ ዕለተ ፍትወት

11. ለፍልሰተ ሥጋኪ፡- በቅድስተ ቅዱሳኑ ቆሞ የድኅነት መሥዋዕትን ያሳርግ ዘንድ ሊቀ ካህናቱን ለአስደሰተው ለአካልሽ ዕርገት ሰላምታ ይገባል፤ እመቤታችን ሆይ! የዕርገትሽ በዓል (ሞገስ) የቂምና የበቀል አለቃ የሆነው የሞት መልአክን ምን ያህል አሳመመው! ምን ያህልስ አደከመው!

12. እም ዓለመ መትሕት፡- ሱራፌ እየጠበቃት በኪሩብ ሀገር ትኖር ዘንድ ከኀላፊውና ከታችኛው ዓለም ለአካልሽ ዕርገት ሰላምታ ይገባል፤ ከታውፊ (መስከረም) ወር አበቦች ይልቅ መዐዛሽ ያማረ እመቤታችን ሆይ! እነሆ በባሕር ጨለማ ዳር ሠጥሜአለሁና በንግሥናሽ (በንጽሕናሽ) መርከብ ሁልጊዜ አሻግሪኝ፡፡

13. ዘአጥናን ኃይሉ፡- የይቅርታው ክንድ ዘለዓለም ትጋትም ኀይሉ ለሆኑ ለአካልሽ ዕርገት ሰላምታ ይገባል፤ ስም አጠራርሽ (ይቅርታሽ) ለትውልድ ጸንቶ የሚኖርልሽ ሆይ! ለዓለም ኀጥአን ምሕረትን ታመጫለሽ፤ የክርስቶስ ወገን የሆንሽ አንቺ ንዕድ ክብርት ነሽ፡፡

14. ዘተወሐዳ፡- እግዚአብሔር ለተዋሐዳትና ክብደቷን ለተካፈላት ለአካልሽ ዕርገት ሰላምታ ይገባል፤ ድንግል ሆይ! በኢየሩሳሌም ዙሪያ ለዕርገትሽ የተርሴስና የደሴቶች ነገሥታት የነጭ ሽቶንና የመታሰቢያ ዕጣንን እጅ መንሻ አድርገው ያገባሉ፡፡

15. ለፍልሰተ ሥጋኪ፡- ከሴሎው ነቢይ ከኤልያስ ዕርገት ይልቅ እግዚአብሔር ከፍ ለአደረገው ለአካልሽ ዕርገት ሰላምታ ይገባል፤ እመቤቴ ማርያም ሆይ! ወደ ጽድቅ ሀገር በፈጣን ነፋስ ክንፍ ውሰጂኝ፤ ሁሉን የሚገዛ ሞት እየተከተለኝ እኔ በጤናና በደስታ ለምን እኖራለሁ፡፡

16. ለፍልሰተ ሥጋኪ፡- ለተመረጡት ልጆች እናታቸው ትሆኚ ዘንድ በረጅም የብርሃን መሰላል ለተደረገው ለአካልሽ ዕርገት ሰላምታ ይገባል፤ እመቤቴ ሆይ! በጭንቅና በረኃብ ወቅት አምስት የድንቢጥ ወፍ ዘሮች በሁለት ጸሪቅ እንደሚሸጡ በይቅርታሽ ጽድቅ ገንዘብ ግዢኝ፡፡

ወጻሕቅ፣ ዘመደ አፅዋፍ ሐምስ በክልኤ ጸሪቅ፡፡

፲፯. ሰላም ለፍልሰተ ሥጋኪ ውስተ ብሔር ሥዑር፡፡ እንተ ኬንያሃ ወገባሪሃ እግዚአብሔር፣ ማርያም ፍትሕኒ እማእሠረ ሞት መሪር፣ ሶበሰ ትፌቅዲ መንግሥተ ሰማያት ወምድር፣ ኢይሰአነኪ አግዕዞቶ ለኃጥእ ገብር፡፡

፲፰. ሰላም ለትንሣኤ ሥጋኪ ዘትንሣኤ ክርስቶስ መንታ፣ ርእሶ ሕያወ እም ድኅረ ኀብአ ውስቴታ፣ በጽላሎትኪ ክድንኒ ማርያም ርግበ ኤፍራታ፣ ወሠውርኒ በአክናፍኪ አመ ይከውን ሐተታ፣ ወአመ ታገብእ ምድር ዘነሥአት ማኅፀንታ፡፡

፲፱. ሰላም ለዕርገተ ሥጋኪ ዘተወጥነ ቦቱ፣ ዕርገተ ቅዱሳን አበው ዘበኀቤኪ ተአኵቱ፣ ለሊቀ ካህናት አሮን ማርያም ሠርጐ ትርሚቱ፣ ሥዑለ ይኩን በልብስኪ እስከነ ላዕሉ ወታሕቱ፣ ፍሬ ከናፍር ወአፍ ውዳሴኪ ዝንቱ፡፡

፳. ሰላም ለጊዮርጊስ ተውላጠ ጻማሁ ወሕማሙ፣ እንተ ተለዓለ ሞገሰ ስሙ፣ በፍልሰትኪ(ተ) ድንግል (ዮም) እንተ ተቶስሐ ፍልሰተ ዓፅሙ፣ እንዘ ይብል ሶበ ጸለየ አሜሃ ቀዲሙ፣ ምስለ ፍልሰትኪ ደምርኒ እሙ፡፡

፳፩. ስብሐት ለኪ ማርያም ለአብ መርዓቱ፣ ስብሐት ለኪ ማርያም ለወልድ ወላዲቱ፣ ስብሐት ለኪ ማርያም ለመንፈስ ቅዱስ ጽርሐ ታቦቱ፣ ወርቅሰ ወብሩር ኃላፊ ውእቱ፣ እም ኵሎን ማርያም ኪያኪ እፌቱ፡፡

አ እግዝእትነ ማርያም ዕቀብኒ ወአድኅንኒ እመከራ ሥጋ ወነፍስ ሊተ ለገብርኪ..... ለዓለመ ዓለም አሜን፡፡

✞ ✞ ✞

17. ለፍልሰተ ሥጋኪ፡- እግዚአብሔር ፈጣሪዋና ጥበበኛዋ ወደሆነላት ወደ ብሔረ ሕያዋን ለተደረገው ለአካልሽ ዕርገት ሰላምታ ይገባል፣ እመቤቴ ማርያም ሆይ! መራራ ከሆነው ከሞት ማሠሪያ ፍቺኝ፣ የሰማይና የምድር ንግሥት ሆይ! ብትወጂስ ኀጥእ ባርያሽን ነጻ ማድረግ አይሳንሽም፡፡

18. ለትንሣኤ ሥጋኪ፡- ሕያው የሆነ ራሱን በውስጧ ከሰወረ በኋላ ለክርስቶስ ትንሣኤ ሁለተኛው ለሚሆን ለአካልሽ ትንሣኤ ሰላምታ ይገባል፣ የኤፍራታ ርግብ እመቤታችን ማርያም ሆይ! በጥላሽ አልብሺኝ፣ ፍርድ በሚሆን ጊዜም አደራሽን በክንፎችሽ ሰውሪኝ፡፡

19. ለዕርገተ ሥጋኪ፡- በአንቺ ዘንድ የከበሩ ቅዱሳን አባቶች ዕርገት ለተጀመረበት ለአካልሽ ዕርገት ሰላምታ ይገባል፣ የሊቀ ካህናት አሮን ሽልማቱ እመቤታችን ማርያም ሆይ! የከንፈርና የአንደበት ፍሬ የሆነው ይህ ውዳሴሽ በልብስሽ ከላይ እስከ ታች ድረስ የተሣለ ይሁን፡፡

20. ለጊዮርጊስ ተውላጠ፡- ለድካሙና ለመከራው ዋጋ ስሙ ከፍ ላለው ለጊዮርጊስ ሰላምታ ይገባል፣ ድንግል ማርያም ሆይ! በዕርገትሽ ዛሬ የዐፅሙ ፍልሰት ተጨመረ፣ ቀድሞ ያንጊዜ ‹ድንግል ሆይ! ፍልሰቴን ከፍልሰትሽ ጋር ጨምሪልኝ› ብሎ ጸልዮ ነበረና፡፡

21. የአብ ማደሪያው የወልድ እናቱ የመንፈስ ቅዱስ የታቦቱ አዳራሽ እመቤቴ ማርያም ሆይ! ሰላምታ ይገባሻል፣ ወርቅና ብር ግን ኀላፊዎች ናቸው፣ ከሁሉም ይልቅ አንቺን እወዳለሁ፡፡

እመቤታችን ድንግል ማርያም ሆይ! ኀጥእ ልጅሽን..... ከመከራ ሥጋ ከመከራ ነፍስ አድኚኝ ለዘለዓለም አሜን፡ :

✞ ✞ ✞

| | |
|---|---|
| | |